ሒጅራ እና ሴቶች

አባቷ አቡበክር በሐሳብ ረዷት ፤ መቀኑቷን ለሁለት እንድትሰነጥቀው መከሯት። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ.) ተግባሯን አደነቁ። በዚህም "ዛት አኒጣቀይን" (ባለ ሁለት መቀኒቷ) በመባል ተሰየመች (አስማዕ አቡበክር)

Telegram – MuhammedNessim
YouTube – Nessim Almuhaba

ታማኝነት እና ሚስጥር ጠባቂነት

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የመሰደድ ፍቃድ ባገኙ ሰዓት ለዝግጅት ወደ አቡበከር ቤት ነበር ያቀኑት። እዛም እንደደረሱ ጉዳዩ ሚስጥራዊ ስለሆነ ለአቡበከር ሲዲቅ (ረ.ዑ.) "አንተ ጋር ያለን ሁሉ አስወጣ፤" አሉት። አቡበከርም "ሁለት ሴት ልጆቼ አሉ፤" በማለት የአላህ መልዕክተኛን አሳወቁ ፤ እነዚህ እንስቶች ሚስጥር ያባክናሉ ብለው እንዳይሰጉ ማረጋገጫ ሰጡዋቸው። የአላህ መልዕክተኛና አቡበከር ሲዲቅ ለመለኮታዊው ስደት አስፈላጊውን ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ጉዞዎቻቸውን ጀመሩ። በአንጻሩ ቀደም ብለው የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ.) ለመግደል ውሳኔ አሳልፈው የነበሩት ቁረይሾት ሴራቸው ስላልተሳካላቸው በደም ፍላት እና በበቀል ጥም እያፈላለጓቸው ይገኛሉ።

የአላህን መልዕክተኛ (ሰ›ዐ›ወ.) እንግደላቸው የሚለውን ሐሳብ አመንጪው የቁረይሽ ባለባት አቡ ጀህል ነበር። የግድያ ፕላኑ ክሽፈት ያንገበገበው አቡ ጀህል ታዲያ በንጋት ተነስቶ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) እና አቡበክር የት እንዳሉ ለመጠየቅ ቀጥታ ያመራው ወደ አቡበክር (ረ.ዓ.) ቤት ነው። እንደደረሰ በሩን ሲቆረቁር ያገኘው

የአቡበክር ልጅ የሆነችውን አስማዕ ቢንት አቡበከር ነበር። በሚያስገመግም ቁጣ የት እንዳሉ እንድትነግረው ጠየቃት። አስማ ግን በልበ ሙሉነት "አላውቅም" ስትል መለሰችለች።

በብስጭት የተከበረውን ውብ ፊቷን በጥፊ መታት። ከንፈሯና ጥርሶቿ ደሙ ፤ ለጆሮ ጌጥነት የምትጠቀምበት ጉትቻዋ ከጆሮዋ ላይ ወልቆ ወደቀ። ነገር ግን መንፈሰ ጠንካራው አስማዕ ካቋሟ ፍንክች አላለችም ፤ በአቡ ጀህል በትር ተረታ ሚስጥሩን አልተናገረችም። በዚህም ሚስጥር ጠባቂነቷን ፣

ሒጅራ እና ሴቶች

ኢስላም ለሴት ልጅ ትልቅ ክብር የሰጠና ደረጃዋን ያላቀ የህይዎት ጎዳና ነው። በተለይም በማህበረሰብ ግንባታ ላይ ትልቁን ሚና የምትጫወትበትን ቁልፍ ለርሷ አስረክቧታል። በዚህም የማህበረሰብ ህልውናን ከመጠበቅ አንጻር በሚደረጉ ትግሎችም ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆና በታሪክ መዛግብት ደማቅ አሻራ ጥላ ማለፍ ችላለች። በነዚህ የታሪክ ምዕራፎች ውስጥ ለዛሬውም ሆነ ለነገዎቹ እንስቶች የሚሆኑ ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ዓብነቶች ታጭቀው ይገኛሉ።

እነዚህን የታሪክ ዓብነቶች አጋጣሚዎችን እየጠበቅን የምናወራቸው ብቻ ሳይሆን ተምሳሌቶቻችን በማድረግ ከታሪክ ምዕራፍ አውጥተን ስጋና አጥንት ለብሰው በኛው ውስጥ እንዲኖሩ ማድረግ ይጠበቅብናል።

በኢስላም ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ካላቸው ቀዳሚ ክስተቶች አንዱ ከመካ ወደ መዲና የተደረገው የነብዩ እና ባልደረቦቻቸው ስደት (ሒጅራ) ነው። ኢስላማዊው የዘመን አቆጣጠርም ይህንን ታሪካዊ ክስተት ተመርኩዞ በጨረቃ መፈራረቅ ላይ የተዋቀረ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም የክስተቱን ታላቅነት ያጎላ ተግባር ነው። ያለንበት ወር የ1437ኛው ሒጅሪያ ዓመት የመጀመሪያ ወር ሙሐረም እንደመሆኑ መጠን ከሂጅራ ጋር የተያያዙ ታሪኮች በስፋት ይወሳሉ። እኔም በቀጣዩ ፅሁፌ በዚህ ታሪካዊ ክስተት ላይ ሴቶች የነበራቸውን ሚና በወፍ በረር ለመቃኘት እሞክራለው።

ሴቶች ለትግል የጋለ ስሜት ያላቸው ፣ ንቁና ፣ ጥንቁቅ መንፈስን የተላበሱ የፀዳ ቀልብ ባለቤቶች ናቸው። ላመኑበት ዕውነት ሚች ከመሆናቸው ጋር የወላዋይነት ስሜት አይታይባቸውም። ስለሆነም ሴት ልጅ ለመነችበት ዓላማ እስከመጨረሻው የመታገል ልዩ ተፈጥሯዊ ተሰጥዖ አላት። ባሏን ፣ ልጆቿን ፣ ወንድሞቿን ባጠቃላይ ቤተሰቧን ባመነችበት ርዕዮተ ዓለም የመቅረፅ ብቃቷ ከፍተኛ ነው። እንስት ሰሃቦች በረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) ዘመን በኢስላማዊ ትግል ውስጥ ይጫወቱት የነበረው ሚና በኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ትልቅ የሴቶች አሻራ ለመኖሩ በቂ ምስክር ነው።

ጽናት፣ ብስለት እና ዘላቂ አብሮነት

የአቡበከር ሲዲቅ አባት የልጃቸውን መሰደድ ሰምተው የልጅ ልጆቻቸውን ሁኔታ ለመመልከት ወደነ አስማዕ ቤት መጡ። በዚህ ወቅት ወቅት አስማ ቢንት አቡበክር በበኩሏ

የሰራችው ስራ ድንቅ ነበር። በአላህ መንገድ ላይ ታብት ንብረታቸውን ሳይሰስቱ የሚያፈሱት አቡበክር ለቤተሰባቸው አንዳች ነገር አስተርፎላቸው ይሆን የሚል ስጋት ገብቷቸዋል። የሚገርመው ከነብያዊው ተልዕኮ መባቻ ጀምሮ ጥሪታቸውን ፈሰስ ቢያደርጉም በዕለተ ሒጅራም ለጉዞው በቂ ዝግጅት የተደረገው በርሳቸው ቤት ነበር። ጉዞው እንደሌላው ጊዜ ሙሉ ቀኑን እና በቀጥታ የሚደረግ ባለመሆኑ የተያዘው ስንቅ በዛ ማለት ነበረበት። ተጨማሪም ካስፈለገ የሚታከለው ከርሳቸው ቤት መሆኑን ስናስብ የአቡበክር አባት ለቀሪ ቤተሰባቸው መጨነቃቸው ተገቢ ነው ያስብላል። ምክንያቱም አቡበክር ለአላህ ለመልዕክተኛው እና በእስላማዊው የዳዕዋ ሒደት ለራሳቸው አንድም ነገር ቀረኝ ሳይሉ ኢንፋቅ ማድረጋቸውን አባታቸው ይቅርና ሁሉም ዘንድ ይታወቅ ነበርና ነው። ይሁን እንጅ ሐፍሳ አያታቸውን ማስጨነቅ እና አባታቸውን እንዴት ባዶ ቤት ጥሎላቸው

ይሄዳል ተብለው በሰው ዘንድ ማሳ'ጣት አልፈለገችም። ለዚህም ስትል ቤት ውስጥ ድንጋይ ሰብስባ በጨርቅ በመሸፋፈን አባታቸው ከመሰደዱ በፊት ለወጪ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ትቶላቸው እንደሄደ አስመስላ አያቷን አረጋጋቻቸው።

አስማዕ እና ሐፍሷ ግን የሚመጣውን ጫና ፣ ችግር እና ፈተና ሁሉ ለመቋቋም በቂ የመንፈስ ዝግጅት አድርገዋል። ባባታቸው እና በነብዩ ስደት ሳይከፉ ለዕውንነቱ የበኩላቸውን ሊያደርጉ ስነልቦናቸውን አሰናድተዋል። ለዚያም ይመስላል ላያታቸው ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ያስቻላቸውን ዘዴ ቀድመው የቀየሱት። ምን የሚያምር ብልኃት ፤ ምን የሚያስቀና ፍጥነት ታድለዋል እነዚህ ሴቶች? ይህን ብስለት እና ነገሮችን በፍጥነት የመዘየድ ክህሎት ባግባቡ ለበጎ ጥቅም ሲያውሉት እንዴትስ ያምራል ባካችሁ። አልሐምዱሊላህ ብዙኃን እህት እና እናቶቻችን ይህን ተሰጥዖ ባለፉት አራት

ዓመታት በገቢር ሲያውሉት ተስተውሏል። እስከዛሬው በያጋጣሚው የታዘብናቸው እና የሰማናቸው ገድሎች እንዳሉ ሆነው ጊዜው ይለፍና የኢትዮጵያውያን እንስቶችን መሰል ክንውን መዳሰሳችን አይቀርም። የአላህ ፈቃዱ ይሁን!!

ጾታ እና ቦታ ያልገደበው ሁለገብ ትብብር

የአላህ መልዕክተኛና አቡበከር ሲዲቅ በዋሻ ውስጥ ተጠልለው በነበሩበት ሰዓት ሁለቱ ልጆቻቸው አብዱላህ ቢን አቡበክርና እህቱ አስማዕ ቢንት አቡበከር ስንቅ በማመላለስና በመካ ያለውን ሁኔታ የሚያስረዳ ትኩስ መረጃን በማቀበል ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ይህ ስጋትን የሚያጭር ፣ ብዙ ርቀትን መጓዝ የሚጠይቅ ፣ በጠራራ ጸሐይ መንገድ አሳብሮ ከጠላት ርቆ መሰወርን የሚሻ ፤ በየዕለቱ ከመደጋገሙ የተነሳ ጉልበትና ወኔን የሚሰልብ ፣ ለአደጋዊ ጥቃት የሚያጋልጥ ሚስጥራዊ ተልዕኮ የተፈጸመው በአስማዕ እና በሐፍሷ ከወንድማቸው ጋር

በነበረ ዓቻዊ ትብብር ነው። እዚህ ላይ ማስተዋል የምንችለው የሴቶች ሚና ከወንዱ ሚና ጋር ተጓዳኝ እና ተደጋጋፊ እንጅ ተለጣፊ እንዳልሆነ ነው። የአስማን ቁርጠኛ መስዋዕትነት እና ለዓላማ ጽኑነት የሚያሳብቀው ሌላኛው ሚናዋ በጉዞው ዋዜማ የነበረው ድንቅ ክስተት ነው።

አባቷ እና ነብዩ ለጉዞው ተነሳስተው ከቀሪ ቤተሰቡ ጋር በመሰነባበቻቸው ምሽት አስማ በአንድ አገልግል ምግብና በሁለት ከረጢቶች ውሀ ሞላች። ለከረጢቶቹ መቋጠሪያ ገመድ ግን በቅርበት አላገኘችም ፤ ማሰሪያ በማጣቷ ግን አላዘነችም። ወዲያውኑ የወገቧን መቀነት ፈታች ፤ የሪቃዋ ጀግና ጸጉሯን ፈትላ በጅሐድ ወቅት ግልጋሎት ላይ ለሚውሉ ፈረሶች ማሰሪያ ይሁንልኝ እንዳለችው ፤ መቀነቷን ለመታጠቂያነት ሳይሆን ለተባረከው ጉዞ ባልደረባችሁ ይሁን አለች። የአስማን ድርጊት የታዘቡት አባቷ አቡበከር በሐሳብ ረዷት ፤ መቀነቱን ለሁለት እንድትሰነጥቀው

መከሯት። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ.) ተግባሯን አደነቁ። በዚህም “ዛት አኒጣቀይን” (ባለ ሁለት መቀነቷ) በመባል ተሰየመች ፤ አብሯት የኖረው እና ዛሬም ድረስ ታሪኳ ሲዘከር የምትታወስበት ቅጽል ስም ወጣላት። በዚህ ታሪካዊ ድንቅ ተግባሯ የሙስሊሙ ዓለም ላይ ለዘላለም ታወቀች።

በስደቱ ወቅት አስማ እርጉዝ ነበረች። ይሁን እንጅ እንደ ሌሎቹ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ሁሉ እርሷም ሆነ ባለቤቷ በመካ የመኖር ፍላጎት አልነበራቸውም። በመሆኑም እርግዝናዋም ሆነ የመንገዱ ርቀት ሳይበግራት ወደ መዲና ለማቅናት አስባ ለጉዞ ተነሳች። በመዲና ዳርቻ ላይ ከምትገኝ ቁባ ከምትባል ስፍራ እንደደረሱ አብደላህ የተባለ ወንድ ልጅ ወለደች። የሒጅራ ታሪክ ሲታወስ አስማ ከሰራችው ሌሎች ጀብዱዎች ጋር ነፍስጡር ሁና ወደ ስደት መውጣቷ እና በጉዞ ላይ አብዱላህን መውለዷ ሁሌም የሚታወስ ነው። በሰላማዊው የሙስሊሙ ህብረተሰብ

ትግል ወቅት በርካቶቹ ነፍሰ ጡር ሆነው አወሊያን ታድመዋል? ታሪክ የማይዘነጋቸው ብዙወቹም አራስ ህጻን ይዘው መብታችን ይከበር ሲሉ አስተጋብተዋል። የወሊድ አልጋ ላይ ሆነው ፣ እርጥብ ህጻን ታቅፈው ባሎቻቸው የታሰሩባቸውንስ እንዴት እንረሳለን። እነኛ የአብራክ ክፋዮቻቸውን ከፍርግርግ ጀርባ ላሉ የግፍ ታሳሪ ባሎቻቸው ያሳዩትስ ስንቶች ናቸው። ስንት ኢትዮጵያዊ ሐፍሳዎች ነፍሰ ጡር ሆነው ከታጋይ እና ኮሚቴ ወንድሞቻችን ጋር አብረው መስዋዕትነት ከፍለዋል። እነኛስ መቼ እንደሚፈቱ ከማያውቋቸው ፣ ባንድ ጎጆ ባይኖሩም ልባዊ ትዳር የመሰረቱት? ከዚህ በላይ አብሮነት ፣ ከዚህ ወዲያ ጽናታዊ ተደጋግፎት የት እናገኝ ይሆን?!

ዛሬ ላይ የቀደምት ትውልድን የሒጅራ ፋና ስናነሳ የኛወቹን አስማዕ እና ሐፍሳዎችን አሻራ አብሮ በመዘከር በመሆኑ ልባችን ይበልጥ ይረካል። የነኛ ሐፍሳ እና አስማዕን

ስራ አላህ እንደወደደላቸው በየዘመናቱ መሰል ታሪክ ለሚሰሩ እህት እናቶቻችን ክብር ይገባቸው። አላህ የነሱንም ሆነ መስዋዕትነትን ሲከፍሉ አብረዋቸው ለቆሙት ወንድሞቻቸው ፣ ልጆቻቸው እና ባሎቻቸው ውዴታውን ይለግስልን - አሚን።

ሒጅራዊ አስተምህሮ ለዘመናችን

አንድ ሙስሊም ማህበረሰብ ማንነታቸውን ያወቁ ፣ በስነ ምግባራቸው የላቁ ፣ የእምነት ጣዕም በልባቸው የሰረፀ ሙስሊም ሴቶችን በውስጡ ካልያዘ አልያም ማፍራት ካልቻለ ኢስላማዊ ገፅታውን መጠበቅ አይችልም። እስልምና የሚገለጽባቸው እሴቶች እና ትውፊቶች በሴቶች ላይ ሲንጸባረቁ በልጆች ፣ ባሎች እና አጠቃላይ ቤተሰቡ ጋር አሻራው ይስተዋላል። ያ ካልሆነ በሌላው ማህበረሰብ ማንነት ጠልቆ ይዘፈቃል። ይህ የማንነት ኪሳራ በማህበረሰባችን መታየቱ አልቀረም። ብዙ እህቶቻችን ከእስልምና ምህዋር ርቀው በተራ የህይዎት ቀመር መሽከርከራቸው

አሳሳቢ ነው። ታዳጊ ልጆቻችንን በእስልምና ማዕቀፍ ውስጥ ማኖር እየተሳነን ያለበት እውነት በግልጽ ይስተዋላል። የሴቶች ስብዕና ሲዋዥቅ የሙስሊሙ ሀልውና ጥያቄ ምልክት ያርፍበታል። ምድር ላይ ኖሮ ከማለፍ ያለፈ ትርጉም ያለው ሀይዎት ሳያጣጥሙ የሚያልፉ ስብዕናዎች ይበረክታሉ። ያ ደግሞ ዘመን ተሻጋሪ እና ሁሏቀፍ ሚና ያልነበረው ግለሰብነትን ያስከትላል። እስልምና ለሁሉም የሰው ልጆች የሚኖረውን የተቀደሰ ፋይዳ ምድር ላይ ሳንጠቀምበት ማለፋችን ለሁለት ዓለም ኪሳራ ይዳርጋል። እንደ ሙስሊም ማህበረሰብም መለኮታዊውን የህይዎት ርዕዮተ ዓለሙ በህብረተሰቡ ውስጥ ማሰራጨት ከባድ ይሆንብናል።

የታብዕዬች ዘመን የሰሐባዎች ዘመን ፍሬ ነው። የሰሐባው ዘመን በረሱል (ሰ›ዐ.ወ.) ስልጠና ተኮትኩቶ ለምጥቀት እንደበቃ ሁሉ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) ውብ አስተምህሮን የቀሰሙ እንስት ሰሐባዎች ምርጡን የታቢዕይ ዘመን

መፍጠር ችለዋል። በአሁኑ ሰዓት በጥልቅ ልናጤነው የሚገባ ጉዳይ የህብረተሰባችንን ከግማሽ በላይ የሚወክሉትን ሴቶች የኢስላምን የተሟላ ፅንሰ ሀሳብ የማስጨበጥ አንገብጋቢነት ነው። ይህን በማድረግ እና በበርካታ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችም ሆነ ትግሎች ላይ የሚኖራቸውን ፋና ለማሳደግ ብዙ ይጠበቅብናል። ሴቶቻችን አስተማማኝ ከሆነ ምንጭ የጠራውን የኢስላም አስተምህሮ እንዲቀስሙ ፣ ምንነቱን ጠልቀው እንዲገነዘቡ ፣ ማራኪ ታሪኩን አንብበው ስብዕናቸውን እንዲቀርፁበት ማድረግ ከተቻለ በታላቁ ኢስላማዊ ክስተት በሆነው ሒጅራ ላይ ያየነውን የሴቶች ሚና ዛሬ ካለው በተሻለ ነገ ላይ የማናይበት ምክንያት አይኖርም።